# ልዑል እግዚአብሔር፥

## የዛሬ ኹለት ሽህ ዐሥራ ኹለት
## ዓመታት፡ በታኅሣሥ አንድ ቀን፡
## ባለሟሉን መልአክ፡ ቅዱስ ገብርኤልን፡
## ወደቅድስቲቱ ኢትዮጵያዊት ድንግል ማርያም ልኮ፡

**"ወናሁ ትፀንሲ! ወትወልዲ ወልደ!**
**ወትሰምይዮ ስሞ፥ 'ኢየሱስ!'"**

ማለትም፡

"እነሆ፡ ትፀንሻለሽ! ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ!
ስሙንም፡ 'ኢየሱስ' ትይዋለሽ!"

ሲል፡ በተናገረው አምላካዊ ቃሉ፡

# "ታላቁን መለኮታዊና ትስብእታዊ
# የዘለዓለም ምሥራች!"

**ለፍጥረተ-ዓለሙ ላሰማባት፥**
**ለዚች፥ ለ፳፻፲፪ (፪ሺ፲፪)ኛዋ**
**የእግዚአብሔራችን ኢየሱስ መሲሕ በዓለ-ትስብእት፥**

እና

ታኅሣሥ ፯ ቀን ለሚውለው፡

**ለእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም፥ የፅንሰቷ በዓል፥**
**በያለንበት፥ እንኳን፥ በደኅና አደረሰን!**

---

# ስለ"ምሥራቹ!"

## ልዩ መግለጫና ማሳሰቢያ!

እስከ፪ሺህኛው የምሕረት ዘመን ድረስ በነበረው፡ በ፩ኛው "ሺህ ዓመት" ውስጥ፡ በጥልቁ፡ ተዘግቶበት ከቆየበት፡ የመለኮት እስራት፡ በ፩ሺ [በ፳፻] ዓመተ ምሕረት፡ ለጥቂት ጊዜ የተፈታው ዲያብሎስ፡ እነሆ፡ አኹን፡ በነጻነት እየሠራ እንደሚገኝ፡ በይፋ ይታወቃል። ከዚህ የተነሣ፡ይህ "ምሥራች!"፡ ዛሬ፡ ከኹለት ሺህ የምሕረት ዓመታት በኋላ፡ በዚህ፡ በ፪ሺህኛው ዐሥራ ኹለተኛ ዓመት ላይ፡ እንደገና፡ እንደአዲስ፡ ሊቀርብና ሊገለጽ፥ ሊነገርና ሊደመጥ፥ ሊጻፍና ሊነበብ፡ እጅግ አስፈላጊ ኾኗል።

አዎን! ይኸው "ምሥራች!"፡ በአካሉና በባሕርዩ፥ በግብሩና በፍሬያማነቱ፡ የማይለወጥ፡ ያው አንዱ፡ ራሱ፥ የጥንቱና የመሠረቱ፥ የመጀመሪያውና ዘለዓለማዊው ቢኾንም፡ ዛሬ የሚቀርብበት መልክና የሚገለጽበት ይዘት፡ በቀደመው ዓይነት ሊኾን አይችልም። እንደዚያ ሊኾን የማይችልበት ምክንያት፡ ያ፡ የቀደመው "ምሥራች!"፡ የተነገረውና የተደመጠው፥ ኋላም፡ የተጻፈውና የተነበበው፡ የሐሰቱ አባት፡ ዘንዶው ዲያብሎስ፡ በእስራት የብረት ወህኒ ውስጥ ተዘግቶበት በተጋዘበት ዘመን ሲኾን፤ ይኸኛው፡ የዛሬው "ምሥራች!" ግን፡ የሚነገረውና የሚደመጠው፥ ከዚያም፡ የሚጻፈውና የሚነበበው፡ ይኸው፡ የክፋቱ አበጋዝ፡ እባቡ ዲያብሎስ፡ እንደመለኮታዊው ቃል፡ ከእስራቱ በተፈታበት ጊዜ በመኾኑ ነው።

ስለዚህ፡ የዚህ ዓመቱ "ምሥራች!" አቀራረብና አገላለጽ፡ የሚገመገመው፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ሰፍኖ ከሚታየው፡ የሰዎች ከኾነችው፡ ከዛሬዪቱ "ዘመናዪት ኢትዮጵያ" እና እርሷ ካፈራችው፡ ከዘመኑ ትውልዷ፥ እንዲሁም፡ ከመላው ሰብአዊ የዓለም ኅብረተሰብ፤ ከፍጥረተ-ዓለሙ ኹኔታና ይዞታ አንጻር፡ ያለውን ትክክለኛ አግባብነት በማሳየት ይኾናል።

እንግዴህ፡ ይህንኑ፡ የዛሬውን "ምሥራች!"፡ ከዚህ አስቀድመን፡ በጎዋ-ሰሌዳችን ዋና ገጽ ላይ፡ በመጽሓፍም ዕትመን ባወጣነው ልዩ መልእክት፡ ገላልጸንና አብራርተን አቅርበነዋልና፡ አኹንም፡ በዚያው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን መንፈስ ኾናችሁ፡ በአትኵሮትና በማስተዋል እንድትመለከቱት ጋብዘናችኋል።

## "በዓለ-ትስብእት" እና "ብሥራተ-ገብርኤል" በሚሉ ስያሜዎች፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን የሚውለው፡ የእግዚአብሔራችን፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ የፅንሰቱ በዓል፡ ታኅሣሥ ፯ ቀን ከሚውለው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከተፀነሰችበት ቀን መታሰቢያ ጋር፡ በታላቅ ሓሜትና በፋሲካ ዝግጅት፥ በእኩለ ሌሊት በሚፈጸም ቅዳሴ፡ የሚከበርበት ሥርዓተ-ጸሎት።

---

**ምንባብ፡-**

ገላ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፩-፯፤
፩ኛ ዮሐ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፯-፲፰፤
ሐዋ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፲፮-፳፫።

**ምስባክ፡-**

መዝ. ፻፴፩፥ ቁ. ፲፫-፲፬፤

| | |
|---|---|
| እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፤ | እግዚአብሔር፡ ጽዮንን መርጧታልና፤ |
| ወአብደራ፡ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፤ | ማደሪያውም ትኾነው ዘንድ ወዷታልና፤ |
| ዛቲ ይእቲ፡ ምዕራፍየ ለዓለም። | ይህች፡ ለዘለዓለም፡ ማረፊያዬ ናት!" አለ። |

**ወንጌል፡-**

ሉቃ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፳፮-፴፰።

### ፍሬ ቅዳሴ

### ቅዳሴ ማርያም።

\+ \+ \+

## <u>የበዓለ-ትስብእት አጭር ዝማሬ</u>

**አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን! (፪ ጊዜያት)**
**መንክር፡ ስብሓተ ትስብእቱ! (፪ ጊዜያት)**
**መንክር፡ ስብሓተ ትስብእታ! (፪ ጊዜያት)**

**<u>ትርጉም</u>**

ዕፁብ ነው! ድንቅ ነው! እውነት፡ በእውነት! (፪ ጊዜያት)
የቃል ሥጋ መኾን፣ በድንግል ሰውነት፡ (፪ ጊዜያት)

## <u>የምሥራች ሰላምታ</u>

በዚህ በዓልና ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ እስከበዓለ-አስተርእዮቱና ጥምቀቱ ድረስ፡
ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡
እርስ በርሳቸው፤ የሚለዋወጡት የምሥራች ቃል፡-

**"ተፈጸመ ትስብእት፡ በማርያም ድንግል!"**
**"በብሥራተ-ገብርኤል፡ ዜናዊ ቃል!"**
ማለትም፡
"የመለኮት ሰው መኾን፡ ተፈጸመ በማርያም ድንግል!"
በአብሣሪው ገብርኤል፡ የምሥራች ቃል!"
እንዲሁም
**"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"**
**በእንተ ትስብእቱ፡ ለእግዚእነ፥ ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ!"**
ማለትም፡
**"ዛሬ፡ ታላቅ ደስታ ኾነ!**
**እግዚአብሔራችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በሰውነት ተፀንሷልና!"**

---

**"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"**
**በእንተ ትስብእታ፡ ለእግዝእትነ፥ ወለመድኃኒትነ ድንግል ማርያም!"**
ማለትም፡
**"ዛሬ፡ ታላቅ ደስታ ኾነ!**
**እግዝእተብሔራችንና መድኃኒታችን ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተፀንሳለችና!"**

# መግቢያ

**"ናሁ፡ ድንግል ትፀንስ! ወትወልድ ወልደ! ወይሰመይ ስሙ፡ 'አማኑኤል!' ዘበትርጓሜሁ፡ 'እግዚአብሔር ምስሌነ!'**

"እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅንም ትወልዳለች፤ 'እግዚአብሔር፡ ከእኛ ጋር ነው!' የሚል ትርጒም ባለው፡ 'አማኑኤል!' በሚልም ስም ይጠራል።" ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ልጇን ወዳጇን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በሰውነት የመውለዷንና የእርሱን፡ በዚህ ዓለም የመገለጡን ተስፋ፡ ነቢያት፡ በጽኑ ጉጉትና ናፍቆት፡ በጾም ተጠምደው፣ በጸሎትም ተመሥጠው፡ ይጠባበቁ እንደነበሩ ይታወቃል።

እኒያ ቅዱሳንና ቅዱሳት ነቢያት፡ በዚህ መልክ፡ አጽንተው የፈጸሙትን፡ ያንን፡ የሱባኤ ትጋሃቸውን በማዘከር፡ እኛ የዛሬዎቹ ወራሾቻቸው የኾንነው፡ ባለዕድሎች ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ ያን፡ የትንቢታቸውና የተስፋቸው ፍጻሜ የኾነውን ጊዜ፣ ይኸውም፡ እርሱን፡ እግዚአብሔር ወልድ ሕፃን ኢየሱስ መሲሕን፡ እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ከመፅነሷ በፊት፡ ያሉትን፡ ፲፭ [ዐሥራ-አምስት] ቀናት፡ "ጾመ-ነቢያት፣ የነቢያት ጾም" ብለን፡ እንጾማቸዋለን። የዚህም ጾም፡ መነሻው፡ ኅዳር ፲፮ ቀን ኾኖ፡ በኅዳር ፴ ቀን ያበቃል። (ኢሳ. ፯፥ ፲፬። ማቴ. ፩፥ ፳፪-፳፫።)

ኅዳር ፲፮ ቀን ተጀምሮ፡ ኅዳር ፴ ቀን በሚያበቃው፡ በዚህ፡ በ"**ጾመ-ነቢያት**" ቀዳሚ አብሣሪነት፣ መንገድ ጠራጊነትና በር ከፋችነት፡ ነፍሳዊው፥ ሥጋዊዉና መንፈሳዊው የንስሓ መሰናዶና የበዓል ዝግጅት ተከናውኖለት የሚከበረው ቀጣዩ በዓል፡ **"በዓለ ትስብእት"** ነው።

ይህ ታላቅ በዓል፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን ከሚውለው፡ ከ"ኢየሱስ መሲሕ ዕለተ-ትስብእት" ተነሥቶ፡ ታኅሣሥ ፯ ቀን በሚውለው፡ በ"እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ዕለተ-ፅንሰት" በኩል ዐልፎ፡ ታኅሣሥ ፴ ቀን፡ "የጥምቀት ከተራ" ተብሎ፡ በዋዜማው፡ የጋድ ጾም እስከሚዘከርበትና ጥር ፩ ቀን እስከሚውለው፥ እስከበዓለ-ጥምቀት ድረስ ባሉት፡ የወሩ ሳምንታት ውስጥ፡ በሓሤት መልክና በፋሲካ ይዘት የሚከበሩትን ንኡሳን በዓላት፥ ከኹሉም በላይ፡ በፍጹሙ የብቅዓት ቅድስና ደረጃ የሚታሰበውን፡ በልማድ፡ "ጾመ ማርያም" የሚባለውን፣ በእውነታው ግን፡ "ህላዌ ማርያም" የኾነውን የህልውና ርእዮትና ዓለም ያካትታል።

**<u>በልማድ፡</u>**

**<u>"ጾመ-ማርያም" የሚባለው ዘይቤ፣</u>**

**<u>በእውነታው፡</u>**

**<u>"ህላዌ ማርያም" ስለመኾኑ።</u>**

በልማድ፡ "**ጾመ-ማርያም**" የሚባለው ዘይቤ፡ በእውነታው ሲታወቅና ሲታይ፡ "**ህላዌ-ማርያም**" ኾኖ ይገኛል። አዎን! "ጾመ-ማርያም"፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰብኣዊው የነፍስና የሥጋ፥ የመንፈስም አካላቷና ባሕርያቷ፡ አካኺዳ የፈጸመችውን ጾም ሳይኾን፡ በዚያን ጊዜ የነበረችበትን፡ የሕያው አኗኗሯን ኹኔታ ገልጾ የሚያሳየው ህልውናዋ ነው።

ይኸውም፡ ራሷ፡ እግዝእተብሔር እም የኾነችው፡ የእግዚአብሔር ወልድ እናት፡ ጥንት በሌለው ቅድምና፡ በመለኮትነት የወለደችውን፡ ይህንኑ መለኮታዊ ልጇን፡ አኹን ደግሞ፡ በኋለኛው የፍጻሜ ሕይወት፡ በሰውነት ለመውለድ፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን በተዋሐደችበት የትስብእት ማሕፀኗ፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ ፀንሳው ሣለች፡ ለ፱ ወሮች ከ፭ ቀኖች፡ የነበረችበት የተዋሕዶ ህላዌዋ፡ ከፍጹምነት የብቅዓት ማዕርግ የደረሰ ኾኖ፡ በመንበረ-ጸባዖት፡ ቅድስት ሥላሴነቷ እና በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፡ ያለችበት፡ የመጨረሻው መለኮታዊና ትስብእታዊ አኗኗሯ፡ እውን ኾኖ መታወቁና መረጋገጡ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ በዘልማድ፡ "ጾመ-ማርያም" የሚል ስያሜ የተሰጠውን ጾም፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የጾመችው፡ "**የመንፈስ ጾም**" በተባለበት የመጨረሻው የፍጹምነት ደረጃው፡ "በመንፈስ ነው!" ቢባልም፡ ያ፡ "የመንፈስ ጾም"፡ ከ"ሥጋ ጾም" እና ከ"ነፍስ ጾም" የተለየ ኾኖ፡ የመጨረሻውን መለኮታዊና ትስብእታዊ ሕያው አኗኗሯን አረጋግጦ የሚያሳውቅና የሚያሳይ እንጂ፡ እንደ"ሥጋ ጾም" እና እንደ"ነፍስ ጾም"፡ የጾም ሥርዓት የተካኼደበትና የተፈጸመበት አለመኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

እኛም፡ ይህንኑ፡ በዘልማድ፡ "ጾመ-ማርያም" የሚባለውን፡ የህልውና ርእዮትና ዓለም፡ አኹን፡ ልንኖረውና ልናሳልፈው የሚገባን፡ "በነፍስና በሥጋ፡ ሊጾምበትም፥ ላይጾምበትም ይቻላል!" የሚለውን ሃይማኖታዊ መርሕ በመከተል፡ እንደእርሷ፡ እንደእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም፡ በዚሁ "'የመንፈስ ጾም' በኾነውና በሚባለው ደረጃ ይኾናል!" ማለት ነው።

ይህም የሚኾነው፡ በቍጥር ፲፫/፳፻፰ቱ መለኮታዊ የዐዋጅ ቃል ውስጥ፡ "የዓመቱ አጽዋማትና በዓላት።" በሚለው ንኡስ ርእስ፣ በ፲፯ኛው አንቀጽ ላይ፡ **"በአጠቃላይ፡ ከመለኮታዊዉና ትስብእታዊው ፅንሰት፥ እንዲሁም፡ አስተርእዮ [መገለጥ] እና የሰማያዊ ፍልሰት ምሥራች የተነሣ፡ በታኅሣሥ ፴ ቀን ከሚጾመው የአንዲት ዕለት ገሀድ [የጥምቀት ዋዜማ ጾም] በቀር፡ ከታኅሣሥ ፩ እስከጥር ፴ ቀን ድረስ ያሉትንና እነዚህን ተከታታይ የመታሰቢያ በዓላት ያካተቱትን፡ ዕለታት የምታከብሩዋቸው፡ ያለጾም፡ በፋሲካ የሓሤት ሥርዓት ይኾናል።"** የሚለውን መመሪያ በመከተል ነው።

## የጾምን ነገር በሚመለከት፡-

የጾም ነገር፡ እዚህ ላይ ከተነሣ ዘንድ፡ የዚህን የጾም ምግባር፡ ሓተታና ማብራሪያ፡ "ጾም"ን በሚመለከት በተጻፉት፡ የመጻሕፍታችን ክፍሎችና የኀዋ መልእክቶቻችን አርእስት ውስጥ እናገኛቸዋለንና፡ እነርሱን መመልከቱ ይጠቅመናል። ከእነዚያ ሓተታዎችና ማብራሪያዎች መካከል፡ አንዱ፡ እዚህ ላይ፡ እንደሚከተለው ተጠቅሷልና፡ እዩት፡-

**ጾም፡** በየግላችን የምናካኺደውን ዓይነት ብቻ ሳይኾን፡ ማኅበራዊዉም ዓይነት ቢኾን፡ በግል ምርጫና ውሳኔ፡ ለየግላችንና በየግላችን የምንፈጽመው ሃይማኖታዊ ምግባር ስለመኾኑ፡ በንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ በተዘጋጀው፡ **"ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት"** በሚለው፡ በ፩ኛው መጽሓፍ፡ በሚበቃ ተብራርቷልና፡ ካስፈለገ፡ እርሱን ማንበቡ፡ በበለጠ ይረዳል።

ነፍስ፡ ወደክፋት ከሚያዘነብሉት፡ ከራሷና ከሥጋዋ ፈቃዳት፡ ራሷን ጠብቃና ተቆጣጥራ፡ የመንፈስን የፍቅር ምዕዳን ተቀብላ እንድትፈጽም የሚያስችላት፡ ታላቁ አምላካዊ ኃይሏ፡ ረቂቁ የጾም ምግባር ሲኾን፡ ይኸው ጾም፡ በሦስት ባሕርያትና ማዕርጋት ተገልጾ፡ በሕያውነት ሲሠራ ይኖራል። ይኸውም፡- **"የሥጋ ጾም"፥"የነፍስ ጾም"** እና **"የመንፈስ ጾም"** ተብሎ ማለት ነው።

የመጀመሪያው ማዕርግ፡ <u>የሥጋ ጾም</u> ነው፤ እርሱም የሚካኼድበት፡ የራሱ መልክና ይዘት አለው፤ ይህን ባሕርዩን የሚያሳየውን እውነታ፡ እንዲህ በሚሉ ቃላት መግለጥ ይቻላል፡-

ነፍስ፡ በራሷ ምርጫና ውሳኔ፡ *ሥጋ*፡ መልካም ለኾነው፡ ለእግዚአብሔራዊው ፈቃድ እንዲገዛ፡ መመሪያዋን አስተላልፋለት፡ እርሱም፡ በተፈጥሮአዊው ግዴታውና ፈቃደኛነቱ፡ ያን መመሪያዋን ተቀብሎ፡ በተግባር እየፈጸመ ለመኾኑ፡ የምታረጋግጥበት ረቂቅ ኃይል፡ የ*ሥጋ* ጾም ጸጋዋ ነው፤ በዚሁ፡ [በ*ሥጋ* ጾም] አማካይነት፡ ነፍስ፡ *ሥጋ*ዋን፡ ባሕርያዊ ፈቃዱ ከኾነው፡ ከመብልና ከመጠጥ፥ ከሌላውም አስገዳጅ ፍላጎቱ ሳይቀር፡ በፈቃዱ እንዲታቀብ በማስቻል፡ ለመንፈስ ፈቃድ እንዲያድር ታደርገዋለች።

በዚህ ዓይነቱ እውነተኛ ጾም፡ **የነፍስ፥ የ*ሥጋ*ና የመንፈስ ፈቃዳት፡ አንድ ይኾናሉ።** የጾም፡ ብቸኛውና መሠረታዊ ዓላማው፡ የአንድ ሰብኣዊ ፍጡር አካላትና ባሕርያት ለኾኑት፡ ለእነዚህ፡ ሦስት የተለያዩ ፍላጎቶች፡ የስምምነት ውሕደትን ማስገኘት ስለኾነ፡ ያ ጿሚ ግለሰብ፡ በዚሁ **የ*ሥጋ* ጾም** ምክንያት፡ በውስጡ፡ ሰላምን አግኝቶ፡ "**ለቀዳማዊው ፍጹምነት**" ይበቃል።

የዚህ ጾም፡ ግልጽ የኾነው መለያ ምልክቱ፡ ***ሥጋ*፡** ተፈጥሮአዊው በኾነው ግዴታው፡ ከነፍስ ባገኘው መመሪያ፡ **የጾምን ጥቅም ዐውቆ፡ ለራሱ ደኅንነት ሲል፡ ራሱን፡ በጾም ቍጥጥር ሥር ማዋልን፡ በፈቃዱ ተቀብሎ መፈጸሙ** ነው። ይህም፡ ከ፷ቱ የዓመት አጽዋማት መካከል፡ ፩ዱ የኾነውን፡ ሕማማትን ጭምር ባካተተው፡ ሁዳዴን በመሰሉት የጾም ወራት፡ እየተካኼደ የሚከናወነውን የጾም ዓይነት፡ በምሳሌነት ብንወስድ፡ ምንነቱንና ጠቃሚነቱን፡ በቀላሉ ልንረዳ ይቻለናል። ይህ፡ "**የ*ሥጋ* ጾም**" ይባላል።

ኹለተኛው ማዕርግ፡ **የነፍስ ጾም** ነው፤ እርሱም የሚካኼድበት፡ የራሱ መልክና ይዘት አለው፤ ይህን ባሕርዩን የሚያሳየውን እውነታ፡ እንዲህ በሚሉ ቃላት መግለጥ ይቻላል፡-

*ሥጋ*፡ የመጀመሪያው ማዕርግ በኾነው፡ በራሱ [የ*ሥጋ*] ጾም አማካይነት፡ ነፍስ ወደበቃችበት፡ ረቂቅ ደረጃ፡ ራሱን፡ እንዲህ፡ ከፍ ስላደረገ፡ የረቡዕና ዓርብ ጾም እንኳ በሌለበት፥ በልቅ የመብልና መጠጥ ብሎት፡ ተገቢ ፍላጎቱን፡ በነጻነት እያረካ፡ የፋሲካውን ወራት፡ ያለጾም፡ ከነፍስና ከመንፈስ ጋር፡ በልዩ ደስታ ያሳልፋል።

**ነፍስ፡ *ሥጋ*ዋን ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥና በቅድሚያ፡ ራሷን ጭምር፡ መልካም ለኾነው፡ ለእግዚአብሔራዊው ፈቃድ፡ ያስገዛች መኾኗን፡ ማረጋገጥ ይኖርባታል።**

ይህም፡ ነፍስ፡ "ክፉ የኾነውን ኹሉ ከማሰብ፥ አስባም ከኾነ፡ ወዲያው፡ በቅጽበታዊ ንስሓ፡ ራሷን ያጸደቀች፥ ያም ካልኾነ፡ ክፉ የኾነውን ኹሉ አስባ ከመናገርና ከማድረግ፡ ራሷን ተቆጣጥራ የገታች፥ ያተረፈችም መኾኗን፡ ለራሷ ማረጋገጥ አለባት!" ማለት ነው። ይህን እውነታ የምታረጋግጥበት ረቂቅ ኃይሏ፡ ይኸው፡ የነፍስ ጾም ጸጋዋ ነው፤ በእርሱ [በነፍስ ጾም] አማካይነት፡ ራሷን ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋዋን ጭምር፡ ባሕርያዊ ፈቃዱ ከኾነው፡ ከመብልና ከመጠጥ፥ ከሌላውም ፍላጎቱ እንኳ ሳይቀር፡ በፈቃዱ እንዲታቀብ በማስቻል፡ ለመንፈስ ፈቃድ እንዲያድር ልታደርገው እንዳልተሣናት ይታወቃል።

እንደዚሁ ኹሉ፡ ይህችው ነፍስ፡ ራስዋን፡ "ክፉ የኾነውን ኹሉ ከማሰብ፥ አስባም ከኾነ፡ ወዲያው፡ በቅጽበታዊ ንስሓ፡ ራሷን ለማጽደቅ፥ ያም ካልኾነ፡ ክፉ የኾነውን ኹሉ አስባ ከመናገርና ከማድረግ፡ ራሷን ተቆጣጥራ ለመገታት፥ ለማዳንም እንደሚቻላት እርግጥ ነው።

የትንሣኤው ወራት፡ እንዲህ፡ የሥጋ ጾም የሌለበት በመኾኑ፥ በዚህ ዓይነቱ የፍሥሓ ጊዜ፡ **የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ ፈቃዳት፡ በከፍተኛ መጠን፡ አንድ ይኾናሉ።** የጾም፡ ብቸኛውና መሠረታዊ ዓላማው፡ የአንድ ሰብአዊ ፍጡር አካላትና ባሕርያት ለኾኑት፡ ለእነዚህ፡ ሦስት የተለያዩ ፍላጎቶች፡ የስምምነት ውሕደትን ማስገኘት ስለኾነ፡ ያ፡ ጿሚው ግለሰብ፡ በዚህ ዓይነቱ **የነፍስ ጾም** ምክንያት፡ በውስጡ፡ ከፍተኛ ሰላምን አግኝቶ፡ አኹን፡ "**ለማዕከላዊው ፍጹምነት**" ይበቃል።

የዚህ ጾም መለያ ምልክቱ፡ ሥጋ፡ በገዛ ፈቃደኝነቱ ጭምር ከተቀበለው፡ **ከሥጋዊው የጾም ቍጥጥሩ በመፈታት፡ የመብልና የመጠጥ ነጻነትን እንደመቀዳጀቱ መጠን፡ ነፍስም፡ በዚያን ጊዜ የምታስበው፥ የምትናገረውና የምታደርገው ኹሉ፡ ከክፉው ኹሉ የነጻ፡ መልካሙ የእግዚአብሔሩ ብቻ የመኾኑ እውነታ** ነው። ይህም፡ ከሌሎቹ አጽዋማት በኋላ፡ በሚከተሉት በታላላቁ በዓላት ሰሞን ከሚደረጉት የፋሲካ ሓሤት ሳምንታት መካከል፡ ለምሳሌ፡ ከትንሣኤ፡ እስከበዓለ መንፈስ ቅዱስ በሚዘልቀው፡ በሰባቱ ሳምንታት ውስጥ እየተካኼደ የሚከናወነውን የፍስክ ህልውና ይመለከታል። ይህ፡ "**የነፍስ ጾም**" ይባላል።

ሦስተኛው ማዕርግ፡ **የመንፈስ ጾም** ነው፤ እርሱም የሚካኼድበት፡ የራሱ መልክና ይዘት አለው፤ ይህን ባሕርዩን የሚያሳየውን እውነታ፡ እንዲህ በሚሉ ቃላት መግለጥ ይቻላል፡-

"**ነፍስ" የተባለችው፡ ዋናዋ የሰውነት አካልና ባሕርይ፡ በምርጫዋና በውሳኔዋ፡ የምታስበውና የምታጸድቀው፥ የምትናገረውና የምታደርገው ኹሉ፡ ከክፉው ኹሉ የነጻውን፡ መልካሙን የእግዚአብሔሩን ብቻ በሚኾንበት ጊዜ፡ ህልውናዋ የሚቀጥለው፡** ክፋትና ጥፋት፥ 'ኃጢአት' የተባለው ሓሰትና ሞትም ተወግደው፡ እንግዴህ ወዲህ በማይገኙበት፥ ነገር ግን፡ በእነርሱ ቦታ፡ ዘለዓለማዊው የትንሣኤ ሓሤትና የሰንበት ተድላ በሰፈነበት፡ በመጨረሻው የመንፈስ ቅዱስ የብቅዓት ሕይወት ውስጥ ስለሚኾን፡ **በዚያ የመንፈስ ሕይወት ውስጥ፡ መጾምም፡ አለመጾምም፥ መብላትም፡ አለመብላትም፡ አስፈላጊነቱ ይቀራል።** ይህም፡ በዚያን ወራት፡ ለመብላት፥ ወይም፡ ላለመብላት፥ ማለትም፡ ከኹለት፡ አንዱን፥ ወይም፡ ኹለቱንም ለመፈጸም ኾነ፡ ላለመፈጸም፡ ይፈቀዳል ማለት ነው።

መጾምም፥ መብላትም በሌለበትና በማያስፈልግበት፡ በዚህ ዓይነቱ ነጻ የጾም ወራት፡ **የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ ፈቃዳት፡ ፈጽመው፡ አንድ ይኾናሉ።**

የጾም፡ ብቸኛውና መሠረታዊ ዓላማው፡ የአንድ ሰብኣዊ ፍጡር፡ አካላትና ባሕርያት ለኾኑት፡ ለእነዚህ፡ ሦስት የተለያዩ ፍላጎቶች፡ የስምምነት ውሕደትን ማስገኘት ስለኾነ፡ ያ፡ ጿሚው ግለሰብ፡ በዚህ ዓይነቱ የመንፈስ ጾም ምክንያት፡ በውስጡ፡ ፍጹም ሰላምን አግኝቶ፡ አኹን ደግሞ፡ "**ለፍጹማዊው ፍጹምነት**" ይበቃል።

የዚህ ጾም መለያ ምልክቱ፡ **ለመብላት፥ ወይም፡ ላለመብላት፣** ማለትም፡ **ለመጠም፥ ወይም፡ ላለመጠም፡ ነፍስ፡ ፍጹም የመምረጥና የመወሰን፥ የማድረግም ነጻነት ያላት መኾኑ** ነው።

ይህም፡ ከዓመቱ ታላላቅ በዓላት የፋሲካ ሓሤት በኋላ፡ ተያይዘው ከሚቀጥሉት አጽዋማት መካከል፡ ለምሳሌ፡ ከታኅሣሥ ፩ እስከጥር ፴ ቀናት ድረስ ከሚካኼደው፡ ከእናቲቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና ከተወዳጁ ልጇ ከኢየሱስ መሢሕ፡ የትስብእት እና የጥምቀት [የአስተርእዮ] በዓላት፡ የፋሲካ ሓሤት በኋላ፡ በሚቀጥለው፡ "ጾመ ማርያም" በተባለው እና ደግሞም፡ ከበዓለ መንፈስ ቅዱስ ማግሥት ጀምሮ፡ እስከሓምሌ ፳ ቀን ድረስ 'ጾመ-ሓዋርያት" ተብሎ፡ በሚዘልቀው ወራት ውስጥ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ በመንፈሳዊው የብቅዓት ህልውናቸው በሚመሠጡበት ጊዜ፡ በመጠምም ኾነ፣ ባለመጠም፡ የሚፈጽሙት የጾማቸው ዓይነት ነው። ይህ፡ "**የመንፈስ ጾም**" ይባላል።

ከዚህ "የመንፈስ ጾም" የምንነት ትርጓሜ የተነሣ፡ እኛም፡ ይህን፡ በዘልማድ፡ "ጾመ-ማርያም" የሚባለውን፡ የህልውና ርእዮትና ዓለም፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ "በነፍስና በሥጋ፡ ሊጾምበትም፥ ላይጾምበትም ይቻላል!" የሚለውን ሃይማኖታዊ መርሕ በመከተል፡ እንደእርሷ፡ እንደእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም፡ በዚሁ የመንፈስ ደረጃ ኾነን፡ ልንኖረውና ልናሳልፈው እንዲገባን፥ እንዲቻለንም ስለተደረገልን፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን ከምናከብረው፡ ከወልደ-እግዚአብሔር ኢየሱስ መሲሕ ዕለተ ትስብእት አንሥተን፤ ታኅሣሥ ፫ እና
፯ ቀናት የምናዘክራቸውን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ሕፃን ድንግል ማርያምን በአተ-መቅደስ እና ፅንሰት፤ እንዲሁም ጥር ፩ ቀን የሚውለውን፡ በዓለ-ጥምቀትን እና ጥር ፯ ቀን የሚታሰበውን፡ የአስተርእዮ-ቅድስት ሥላሴን በዓል፤ ደግሞም፡ ጥር ፳፩ ቀን የሚከበረውን፡ "አስተርእዮ" የሚባለውን፡ የፍልሰታ ለማርያምን በዓል ዐልፈን፡ **የሦስቱ ዕለታት የኢትዮጵያ በዓል** ማብቂያ እስከኾነው፡ እስከጥር ፴ ቀን ድረስ ያለውን፡ የኹለት ወራት ጊዜ፡ በሥጋችንና በነፍሳችን፥ በመንፈሳችንም፡ በፍጹም የፋሲካ ዝግጅትና ሓሤት፥ ፍቅርና ሰላም እናሳልፈዋለን።

## ዕለተ-ትስብእት።

"ትስብእት"፡ "ቃል፡ ሥጋ ኮነ! ቃል፡ በተዋሕዶ፡ ሥጋ ኾነ!" ወይም፡ "'ቃል' የተባለው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በተዋሕዶ፡ ሰው ኾነ!" ማለት ነው።

አዎን! "ትስብእት"፡ እግዚአብሔር፡ በተዋሕዶ፡ ሰው የመኾኑ ትንቢት፡ የተፈጸመበት፥ ምስጢሩም፡ የተገለጸበት፡ የመለኮት፡ ዕፁብ ድንቅ ሥራ ነው፤ ባጭሩ፡ የ"ምስጢረ-ሥጋዌ' ሌላው ስሙና ገጽታው ነው!" ሊባል ይቻላል።

የ"ትስብእት" ትርጉም፡ እንዲህ በሚል፡ በአንድ ዐረፍተ-ነገር ይጠቃለላል፡- **በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓደቻት፡ ኢትዮጵያዊቷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ያለሰብኣዊ ወንድ ዘር፡ በድንግልናዋ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ በሰውነት የወለደችው፡ እግዚአብሔር ወልድ፤ እርሱም፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በምስጢረ-ተዋሕዶ፡ "ከኹለት አካላት፡" ማለትም፡ "ከመለኮትና ከሰውነት አካላት፡ አንድ አካል፤ ከኹለት ባሕርያት፡" ማለትም፡ "ከመለኮትና ከሰውነት ባሕርያት፡ አንድ ባሕርይ ኾነ!" ማለት ነው።** (ዮሓ. ምዕ. ፩።)

በእውነተኛውና በትክክለኛው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን የሚውለው "ዕለተ-ትስብእት"፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሊቀ - መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ የምሥራች ቃል፡ እግዚአብሔራችንን ኢየሱስ መሲሕን፡ የፀነሰችባት ዕለት ናት።

በዚች ዕለት፡ እግዚአብሔር፡ በመልኩ ለፈጠረው የሰው ዘር ያዘጋጀው፡ ይህ ታላቅ ቸርነቱ፡ ይፈጸምባት ዘንድ ወድዶ፡ በነፍሷም፥ በሥጋዋም፥ በመንፈሷም፡ ራሷን፡ ለዚህ የንጽሓ ባሕርይ ክብር አብቅታ ስለተገኘች፡ በመረጣት፡ በዚችው ቅድስት ድንግል ዘንድ፡ የኾነውንና የተደረገውን ድንቅ ነገር፡ ዝክረ-ነገሩ፡ ሲወርድ ሲዋረድ በደረሰን፡ እንዲህ በሚለው የትውፊት ቃል እንጀምርላችኋለን፡-

"'**ናሁ ድንግል ትፀንስ! ወትወልድ ወልደ!** እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች! ወንድ ልጅንም ትወልዳለች!' ተብሎ፡ በነቢያት የተነገረው ትንቢት፡ የሚፈጸምበት ጊዜ ሲደርስ፣ ማለትም፡ የ፭ሺ፭፻ ዓመተ ኵነኔ ዘመን ሲፈጸም፡ እግዝእተብሔራችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ "ውኃ ስትቀዳ" ይላል፥ "በቤተ ዮሴፍም' ይላል፥ "በቤተ-መቅደስም" ይላል፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ '**ትፀንሲ!** ትፀንሻለሽ!' አላት።

"ይህ እንደምን ነው?" ቢሉ፡ ኹሉም ተደርጓል። ከኢትዮጵያውያት ወገኖቿ ደናግል ጋራ፡ ውኃ ልትቀዳ ኼዳ፡ ስትመለስ፡ የተጠማ ውሻ ስላገኘች፡ ከቀዳችው ውኃ ቀንሳ፡ አጠጣችው። 'ርኅርኅተ-ልብ' ያሰኛት፡ አንዱ ምግባርዋ፡ ይህ ነው። በዚህ ጊዜም፡ ዐብረዋት ከነበሩት ደናግል መካከል፡ አንዳንዶቹ፡ 'እኅቴ! ይህን ያህል ርኅራኄ፡ እንዴት ነው? «በዚህ ወራት፡ ‹አምላክ፡ ከድንግል ይወለዳል!› ይባላል፤» ከአንቺ ይኾን?' አሏት።

"ወዲያው፡ መልአኩ ተገልጦ፡ '**ትፀንሲ!** ትፀንሻለሽ!' አላት። ዝም ብላ ኼደች። ከቤት ደርሳ፡ ውኃውን ስታወርድ፡ መልአኩ እንደገና፡ '**ትፀንሲ!** ትፀንሻለሽ!' አላት። 'ይህ ነገር ደጋገመኝ! እስኪ፡ ከቤተ-መቅደስ ኼጄ ልረዳው!' ብላ፡ ከእነዚሁ ወገኖቿ ድናግል ጋራ፡ ተካፍላ፡ እያስማማች የምትፈትለው፡ ሐርና ወርቅ ነበር፤ ያን ይዛ፡ ወደቤተ-መቅደስ ኼደች። በቤተ-መቅደስ ተቀምጣ፡ ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል፡ አኹንም እንደገና፡ '**ትፀንሲ!** ትፀንሻለሽ!' አላት።

ይህን ያላት፡ ይህ መልአክ ማነው? ይህ ነገር ከመኾኑ፡ ከስድስት ወራት በፊት፡ ካህኑ ዘካርያስ፡ በቤተ-መቅደስ፡ እያገለገለ ሣለ፡ ሚስቱ ኤልሣቤጥ፡ መጥምቁ ዮሐንስን፡ የምትፀንስ ስለመኾኗ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ የመጣለትን መልእክት ያበሠረው መልአክ ነው።

መልአኩ፡ ይህን ምሥራች፡ ለዘካርያስ ሲነግረው፡ ዘካርያስ፡ የመልአኩን ቃል በመጠራጠሩ፡ "**አነ ውእቱ ገብርኤል፡ ዘእቀውም ቅድመ እግዚአብሔር! ተፈኖኩ ኀቤከ፤ እንግርከ፤ ወእዜኑ፡ ዘንተ።** ይህችን ምሥራች፡ እነግርህ ዘንድ የተላክሁት እኔ፣ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ!" ያለው፡ ሊቀ-መላእክት ነው።

ይኸው መልአክ፡ ይህን ምሥራች፡ ለዘካርያስ ነግሮት፡ ኤልሣቤጥ ከፀነሰች፡ ከስድስት ወራት በኋላ፡ በዚች ዕለት ደግሞ፡ ለድንግል ማርያም፡ በቤተ-መቅደስ ተገልጦላት፡ በሦስተኛው ጊዜ፡ እንዲህ ሲል አበሠራት፡- "**ወናሁ ትፀንሲ! ወትወልዲ ወልደ! ወትሰምዪዮ ስሞ፡ 'ኢየሱስ!' ውእቱ ዐቢይ፤ወይሰመይ፡ 'ወልደ-እግዚአብሔር ልዑል።' ወይሁቦ እግዚአብሔር አምላክ፡ መንበረ-ዳዊት አቡሁ፤ ወይነግሥ፡ ለቤተ-ያዕቆብ ለዓለም፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።**

"እነሆ ትፀንሻለሽ! ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ! ስሙንም፡ 'ኢየሱስ' ትዪዋለሽ! እርሱ፡ ታላቅ ነው፤ 'የልዑል እግዚአብሔር ልጅ' ይባላልም። እግዚአብሔር አምላክ፡ የአባቱን፡ የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋልም፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ፡ ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱ፡ መጨረሻ የለውምም።'

በዚህ የምሥራቹ ቃል፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ከእርሷ፡ ከእግዝእተብሔር ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሰው ኾኖ የመወለዱን ምስጢር፡ ከእግዚአብሔር መንግሥት ምንነት ጋር፡ አብራርቶ አሳወቃት።

እርሷም፡ "**እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ፡ እንዘ ኢየአምር ብእሴ? እፎኑ ይከውነኒ?** ወንድ ስለማላውቅ፡ ይህ፡ እንዴት! እንዴት! ሊኾንልኝ ይችላል?" ብላ መልሳ፡ በልቧ ያለውን፡ የእውነት ጥያቄ አቀረበችለት። ድንግል ማርያም፡ ይህን ጥያቄ፡ ለመልአኩ ማቅረቧ፡ ተጠራጥራው አይደለም፤ "እኔ፡ ይህን ነገር፡ እንኳንስ ላደርገው፡ ስለማላስበውም፡ እንደምን ሊኾን ይችላል?" ስትለው ነው።

መልአኩም፡ "**መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ፡ ይመጽእ ላዕሌኪ፤ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ፤ ወዘኒ ይትወለድ እምኔኪ፡ ቅዱስ ውእቱ፤ ወይሰመይ፡ ወልደ-እግዚአብሔር ልዑል። ወናሁ ኤልሣቤጥኒ፡ እንተ እምአዝማድኪ፡ ይእቲኒ ፀንሰት፣ ወረከበት፡ ወልደ፣ በልህቃቲሃ፣ ወበርስአቲሃ። ወናሁ፡ ሳድስ፡ ዝንቱ ወርኅ፡ ለእንተ ይብልዋ፡ 'መካን!' እስመ አልቦ ነገር፡ ዘይስአኖ ለእግዚአብሔር።**

"መንፈስ ቅዱስ፡ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይዋሓድሻል፤ ስለዚህም፡ ከአንቺ የሚወለደው እርሱ፡ ቅዱስ ነው፤ 'የልዑል እግዚአብሔር ልጅ' ይባላልም።

"እነሆ! ከዘመዶችሽ መካከል፡ አንዷ የኾነችው ኤልሣቤጥም እንኳ፡ በዚህ፡ በላቀ የዕርጅና ዕድሜዋ፡ ወንድ ልጅን ፀንሳለች፤ 'መካን!' ትባል ለነበረችው፡ ለእርሷ፡ ይህ፡ ስድስተኛ ወርዋ ነው፤ ለእግዚአብሔር፡ የሚሳነው ነገር የለምና!" የሚለውን፣ ሌላ ጥያቄ ሊያስከትል የማይችለውን አጥጋቢ ምላሽ ሰጣት።

እርሷም፡ ከዚያ በኋላ፡ ወዲያ ወዲህ የማያሰኘውን፡ ይህን፡ መልአካዊ መልስ ስላገኘች፡ አፍአዊውና ውሳጣዊው ኹለንተናዋ ረክቶ፡ ወዲያው፡ "**ነየ አመተ-እግዚአብሔር! ይኩነኒ፡ በከመ ትቤለኒ!** እነሆኝ! የእግዚአብሔር አገልጋይ [ገረድ]! እንዳልኸኝ ቃልህ ይኹንልኝ!" ብላ፡ መለኮታዊዉን መልእክት ለመቀበል፡ ፍጹም ዝግጁነቷንና ቍርጥ ፈቃደኝነቷን፡ ለሰማያዊው መልእክተኛ አሳወቀችው።"

ልክ፡ በዚች ዕለት፣ ከዕለቷም፡ ይህን ቃሏን፡ ከልቦናዋ አፍልቃ፡ በአንደበቷ ባሰማችባት፡ በዚያች ቅጽበት፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በማሕፀኗ ተፀነሰ።

ስለዚህ፡ **ፈጣሪ፡ ፈቃዱ ኾኖ፡ እንደተስፋ ቃሉ፡ አምላካዊ አካሉንና ባሕርዩን፡ በንጽሕት ድንግል ማሕፀን ውስጥ፡ መለኮታዊቷ እግዚአብሔር እም፡ ከተዋሓደችው፡ ከፍጡሩ ሰብአዊ አካሏና ባሕርይዋ ጋር አዋሕዶ፣ ማለትም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፣ ከነፍሷም፡ ነፍስን፣ ከመንፈሷም፡ መንፈስን ነሥቶ፡ በፍጹም የሰውነት ትስብእት፡ የተፀነሰባት፡ ይህች፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን፡ "ዕለተ-ትስብእት" ተብላለች።**

**"ዕለተ-ትስብእት"** የተባለችው፡ ይህችው፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በማሕፀኗ ተፀንሶና ተሠግዖ፡ ከእርሷ፡ በሰውነት የሚወለድ፡ የመኾኑን ምሥራች፡ ሊቀ -መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ ከእግዚአብሔር ተልኮ፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ያሰማባት ዕለት ስለኾነች፡ "ብሥራተ-ገብርኤል" ተብላም፡ በታላቅ ክብርና ሓሤት፡ ትዘከራለች፤ ትከበራለች።

በያመቱ፡ "ብሥራተ ገብርኤል" ተብሎ፡ በታኅሣሥ ፳፪ ቀን፡ በከፍተኛ ድምቀትና ሥርዓት ሲከበር የቆየው፥ አኹንም፡ እየተከበረ ያለው በዓል፡ የእግዚአብሔራችንና የሰላማችን፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ የፅንሰቱ፥ የትስብእቱ ዕለት፡ በዚሁ፡ በታኅሣሥ ወር ውስጥ ለመኾኑ፡ ማረጋገጫ ኾኖ፡ በቂ ማስረጃነቱና ምስክርነቱ፡ በዐዋጅ ሲናገር ይኖራል።

በግእዝ፡ "ብሥራት"፥ በኢትዮጵያኛ፡ "ምሥራች" ማለት ነው። (ሉቃ. ፩፥ ፲፱፤ ፳፮፥ ፴፩-፴፰። (ኢሳ. ፯፥ ፲፬። ማቴ. ፩፥ ፳፪-፳፫።)

# ፅንሰታ ለማርያም።

የቅድስት ድንግል ማርያም፡ አዛውንት ወላጆች፡ ኢያቄምና ሓና፡ መኻኖች በመኾናቸው፡ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር፡ ልጅ እንዲሰጣቸው፡ በሃይማኖት ተስፋ ጸንተው፤ በጾም፥ በጸሎትና በምጽዋት ምግባራትም ተወስነው ከኖሩ በኋላ፡ የለመኑትን፡ የማይነሣው፥ የነገሩትንም፡ የማይረሳው፡ ይኸው አምላካቸው፡ በሃይማኖታዊ ምግባራቸው፡ ለፍጹምነት የበቃውን፡ ልመናቸውን ተቀብሎ፡ የሓናን ማሕፀን፡ ለአምላክ እናትነት የተመረጠችውን፡ ድንግል ማርያምን፡ ይፀንስ ዘንድ፡ በቅድስናው ከፈተ!

እግዚአብሔራችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ከመፀነሱ፡ ከ፲፮ (ዐሥራ-ስድስት) ዓመታት በፊት፡ እርሱን፡ ቀድሞ፡ በመለኮቱ የወለደችው፡ እግዝእተብሔር እም፡ አኹን ደግሞ፡ በሰውነት የምትወልድባት ድንግል ማርያም፡ በታኅሣሥ ቀን ተፀነሰች። ያችም ዕለት፡ "ፅንሰታ ለማርያም" ተባለች።

ዕፁብ ድንቅ መለኮታዊ ሥራ ስለኾነው፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያም ፅንሰት፡ በትውፊት ያገኘነው ዝክረ ነገር፡ እንዲህ ይላል፦

"የድንግል ማርያም፡ የምዝላቶቿ ምዝላቶች ከኾኑት፡ ከኢትዮጵያ ልጆች የተገኙት፡ ቅድመ-ቅድም አያቶቿ፡ 'በጥሪቃ' እና 'ቴክታ' ይባላሉ። 'ይህ ቀራቸው!' የማይባሉ፡ ባለጸጎች ነበሩ።

"ሀብታቸውም፡ በወርቅና በብር ሚዛን፥ በቀንድና በጋማ ከብት መጠን ብቻ የሚወሰን ሳይኾን፡ በወንድና በሴት አገልጋዮችና ሠራተኞች ብዛትም ጭምር የሚለካ ነበር፤ አንዱን ዓይነት፡ በምሳሌነት ለመጥቀስ፡ ከብዛቱ የተነሣ፡ ወርቁን፡ እንደአምባር እና እንደቀለበት እያሠሩ፡ ከበሬው እና ከላሙ ቀንድ ላይ ያጠልቁት ስለነበር፡ የወርቁም፥ የከብቱም ብዛት፡ ይህን ያህል፡ 'አቅርንተ-ወርቅ' (የወርቅ ቀንዶች)፥ ይህን ያህል፡ 'አቅርንተ-ብሩር' (የብር ቀንዶች) ተብሎ ይቆጠር ነበር እንጂ፡ የቀረው አይቆጠርም ነበር።

"ከዕለታት አንድ ቀን፡ በጥሪቃ፡ ገንዘባቸው ከሚገኝበት ግምጃ ቤቱ ገብቶ፡ የገንዘቡን ብዛት ከተመለካከተ በኋላ፡ ሚስቱን፡ እንዲህ አላት፦ 'ቴክታ! እኔ መኻን! አንቺ መኻን! ይህ ኹሉ ገንዘብ፡ ለማን ይኾናል?'

"'እርሷም፡ 'እግዚአብሔር እንጂ፡ ከእኔ ባይሰጥህ፡ ወይ፡ ከሌላ ሴት ፍሬን ይሰጥህ ይኾናልና፡ ለምን፡ ሚስት አግብተህ፡ አትወልድም? አለችው።

"እርሱም፡ 'ይህንስ፡ እንዳላደርገው፡ የአባቶቻችን ኢትዮጵያውያን እና የእናቶቻችን ኢትዮጵያውያት አምላክ ያውቃል! አንቺስ፡ ይህን ስሑት ነገር፡ እንዴት አሰብሽው? አኹንም፡ እኅቴ! ይህንኑ ጥፉ አሳብሽን፡ በዚችው ቅጽበት፡ በንስሓ አስወግጂው!' አላት።

"[ባሏ በጥሪቃ፡ ይህን ያላት፡ ያለምክንያት አልነበረም፤ እኒህ ባልና ሚስት፡ ኹለቱም፡ በኢትዮጵያ ልጅነታቸው የሚኖሩበት የህልውና ሥርዓት፡ ከአንድ በላይ፡ ሚስቶችን ማግባት እንደሚፈቅደውና የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚጨምረው፡ እንደሌሎቹ የአረማውያንና የአሕዛብ ልማድ ሳይኾን፡ እግዚአብሔር፡ በአዳም እና በሔዋን የትዳር ኑሮ የመሠረተው፡ አንድ ወንድ፡ በአንዲት ሴት፣ አንዲት ሴት፡ በአንድ ወንድ ብቻ ተወስነውና በዚሁ ጸንተው እንዲኖሩ የሚያሳስበው የጋብቻ ቃል ኪዳን የሚጠበቅበት በመኾኑ ነው።]

"በዚህ ጊዜ፡ ኹለቱም ስላዘኑበት፡ ስለዚሁ ችግራቸው፡ ለሚያመልኩት ፈጣሪያቸው ለማመልከት ተስማምተው፡ በእየፊናቸው፡ ሱባኤ ገቡ። ወዲያው፡ ከሌሊቱ በአንዱ፡ ኹለቱም፡ አንድ ራእይ አይተዋል፤ ራእያቸውም፡ ይህ ነው፦ 'ነጭ እንቦሳ፡ ከበረታቸው ስትወጣ፣ እንቦሳዪቱ፡ እንቦሳን እየወለደች፡ እስከስድስት ስትደርስ፣ ስድስተኛዪቱ፡ ጨረቃን፣ ጨረቃ፡ ፀሓይን ስትወልድ አይተው፡ ወደመፈክረ-ሕልም (ሕልም-ፈቺ) ኼደው ነገሩት። እርሱም፡ 'ደግ ልጅን ትወልዳላችሁ! ከዚያም፡ እስከ ስድስት ትውልድ፡ እንደእርሷ፡ ደጋግ የኾኑ፡ የልጅ-ልጆችን ታገኛላችሁ! ስድስተኛዪቱ፡ «ጨረቃ»፡ ከፍጡራን በላይ የምትኾን ልጅን ትወልዳላችሁ! የሰባተኛዋ፡ የ«ፀሓይ» ነገር፡ ግን፡ አልተገለጸልኝም፤ እንደነቢይ/ነቢይት፣ እንደንጉሥ/ንግሥት ያለ ይኾናል!' አላቸው።

"እነርሱም፡ 'ጊዜ ይተርጉመው!' ብለውት፡ ወደቤታቸው ተመለሱ። ከዚህ በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ የባልና ሚስቱን፡ የኀዘን ጸሎት ሰማ፤እነሆ፡ ቴክታ ፀነሰች! ሴት ልጅንም ወለደች! 'ምኞቴ፡ ተፈጸመልኝ! ስእለቴም፡ ደረሰልኝ!' ስትል፡ ለዚች የስእለት ልጇ፡ 'ሄኤሜን' የሚል ስምን አወጣችላት። ሄኤሜንም፡ ሴት ልጅን ወለደች፤ ይህች ልጇም፡ የልጅ ልጅን አይታ፡ ያች የወለደቻት ልጅ፡ 'ሄርሜላ' ተብላ፡ እርሷ ደግሞ፡ የድንግል ማርያምን እናት፡ 'ሐና'ን ወለደች።

"ኢትዮጵያዊቷ ሐና፡ አካለ-መጠን ስታደርስ፡ ከቤተ-ይሁዳ ለተወለደው፡ 'ኢያቄም' ለሚባል፡ ኢትዮጵያዊ ደግ ሰው አጋቧት። ምክነት፡ የምዝላቶቿ ምዝላቶች ከኾኑት፡ ቅድመ-አያቶቿ ወርዶ፡ እርሷ ላይ ሲደርስ፡ እንደነርሱ፡ መኻን ኾነች። ከዚያውም ጋር፡ በሀብቱ ቦታ፡ ደህነቱ ተተክቷል። ይህንም እውነታ፡ ከዚህ የሚከተለው ዝክረ-ነገር ያረጋግጣል።

"የደህነታቸው መጠን፡ ወደምን ዓይነቱ ዝቅተኛ ደረጃ እንደወረደ የሚያሳየው ኹኔታ፡ ሓና፡ ወደውጭ ለብሳ የምትኼደው ልብስ እስከማጣት መድረሷ ነበር፤ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮዋ፡ ለመሳለምና የተለመደ ጸሎቷን ለማድረስ እንኳ፡ ወደእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ ለመኼድ ካልቻለችበት ችግር ላይ ወድቃ ነበር።

"በእንደዚህ ያለ ኹኔታ ላይ ሣለች፡ ከዕለታት አንድ ቀን፡ የምትወድደው በዓሏ የኾነውን ዕለት ለማክበር ይኹን፥ ወይም፡ በልቡናዋ ያለውን ምኞቷን ይፈጽምላት ዘንድ፡ ስእለቷን፡ ለአምላኳ ልታቀርብ፥ ወይም፡ በሌላ፡ ባልታወቀ፡ የሚገፋፋ ምክንያት፡ በግድ፡ ወደእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ ለመኼድ ፈልጋ ተነሣች። ነገር ግን፡ ለዚያ ልዩ ዕለት የሚኾን፡ ማለፊያ ልብስ ስላልነበራት፣ ይህም ማጣቷ፡ ከዚያ፡ ካሰበችው ዓላማዋ፡ ሊያስቀራት የሚችል ምክንያት ኾኖ ስላገኘችው፡ እጅግ አዘነች።

"ይህን ችግሯን ለማስወገድ ስለምትችልበት መንገድ፡ ኀዘንን በተሞላ ልቡናዋ ተክዛ፡ ስታወጣና ስታወርድ ሣለች፡ በግልሙትና የምትኖር፡ አንዲት ጎረቤቷ አይታት ኖሮ፡ 'ሓና! ዛሬ፡ ምን ኾነሻል? በከባድ ኀዘን ተክዘሽ አይሻለሁ፤ ምነው?' አለቻት።|

"ሓና፡ ለዚህ፡ ለጎረቤቷ ጥያቄ፡ መልስ ለመስጠት፡ የመጣላት መፍትሔ፡ አንድ ብቻ ኾኖ አገኘችው፤ እርሱም፡ ይህንኑ ችግሯን፡ ለዚችው ጎረቤቷ ማዋየት ነበር። እርሷም፡ በዚሁ አሳቧ ቆርጣ፡ እንዲህ ስትል፡ ችግሯን፡ ለዚያችው ጎረቤቷ አዋየቻት፦ 'ዛሬ፡ ወደቤተ-እግዚአብሔር ኼጄ፡ ‹እሳለማለሁ!› ብዬ አስቤ ነበር፤ ነገር ግን፡ ለብሼው የምኼደው ልብስ ስለሌለኝ፡ ልኼድ የምችል አልመሰለኝም፤ ለዚህ ነው።'

"ያች ጎረቤቷም፡ 'ልብስማ! የእኔ፡ ከአንድ፣ ኹለት፣ ሦስት፡ አለልሽ አይደለምን? ለምን፡ ከእነዚያ፡ አንዱን መርጠሽ፡ ያን ለብሰሽ አትኼጅም?' አለቻት።

"ሓናም፡ በቅን ኅሊና፡ በየዋኅ ልቡናና በትሑት ሰብእና፡ 'አይ! ያማ! አይኾንም፤ የአንቺ ልብስ እኮ የተገዛው፡ በዐስበ ደነስ (በኃጢአት፥ በግልሙትና ዋጋ) በተሰበሰበ ገንዘብ ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ፡ ንጹሓ ባሕርይ ነውና፡ ንጹሕ ነገርን ይወድዳል፤ ይህን፡ የአንችን ልብስ ለብሼ ብለምነው፡ ‹እንዴት ይሰማኛል!› ብዬ ነዋ!' አለቻት።

"ሴቲቱም፡ 'ሓና! እኔ፡ ‹በምን ምክንያት፡ አምላክ፡ ሓናን፡ ልጅ ነሣት?› እያልሁ፡ ሳዝንልሽ እኖር ነበር፤ ለካ! እንዲህ፡ እንደድንጋይ አድርቆ ያስቀረሽ፡ ይህ ክፋትሽ ኖርዋልና!' አለቻት።

"ሓናም፡ በዚህ እጅግ አዘነች።

"ይህን ኀዘኗን የሚያባብስ፡ ሌላ ድርጊት ደግሞ አጋጠማት፤ ይህም፡ ካላሰበችው አግጣጫ የተሠነዘረ ነበር። ሓና፡ ያላትን፡ ያንኑ ልብሷን አጽድታ፡ ከባሏ፡ ከኢያቄም ጋር፡ ኹለቱም ኹሉ፡ 'ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕት እናቀርባለን!' ብለው፡ ወደቤተ-መቅደስ ኼዱ።

"ሊቀ -ካህናቱ፡ 'ሮቤል' ይባላል፤ እርሱም፡ 'እናንተማ! «ብዙ! ተባዙ!» ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ ለአዳም እና ለሔዋን የሰጣቸውን፡ የበረከት ቃል ያስቀረባችሁ፡ ርጉማን አይደላችሁምን? ቢጠላችሁ ነው እንጂ፡ ቢወድዳችሁማ! ልጅን ይሰጣችሁ አልነበረምን? ስለዚህ፡ መሥዋዕታችሁን አልቀበልም!' ብሏቸዋል።

"ከዚህ በቀር፡ ከኪዳነ ኦሪቱ አማኞች መካከል፡ ሽማግሎች የኾኑ ወላጆች ብቻ የሚመገቡት፡ ተረፈ-መሥዋዕት (ከመሥዋዕቱ የሚተርፍ) ነበር፤ ያንንም እንዳይሳተፉ፡ ይኸው ሊቀ ካህናት ከልክሏቸዋል። በዚህ ኹሉ በደል፡ ተደራራቢ ኀዘን ደርሶባቸው፡ በትካዜ ኾነው፡ ወደቤታቸው ተመለሱ።

"ከቤተ-መቅደስ ሲመለሱ፡ በመንገዳቸው ላይ፡ እንዲህ፡ በኀዘን፥ በትካዜ ተውጠው፡ ከዛፍ ጥላ ሥር፡ ዐረፍ ብለው ሣሉ፡ ሓና፡ ርግቦች፡ ከልጆቻቸው ጋር፡ በወላጅነት ፍቅር፡ የሚያደርጉትን ጨዋታ፣ ዛፎቹም፡ አብበውና አፍርተው፡ የሚያሳዩትን፡ የሥነ-ፍጥረት ውበት ተመልክታ፡ 'አቤቱ! ርግቦችን፡ በባሕርያቸው እንዲዋለዱ፥ ዕፅዋትንም፡ በተፈጥሮአቸው እንዲያብቡና እንዲያፈሩ የምታደርግ አምላክ፡ የእኔ፡ ምንነቴ፡ ከደንጊያ የተሠራ ይመስል፡ ልጅ የነሣኸኝ፡ ለምን ይኾን?' ብላ አዘነች።

"ኹለቱም፡ ከቤታቸው ሲገቡ፡ ተነጋገሩና፡ 'ወንድ ልጅ ብንወልድ፡ «ወጥቶ ወርዶ፥ አርሶ ቆፍሮ፡ ይርዳን!» አ'ንልም፤ ለቤተ-እግዚአብሔር፡ አንጣፊ፣ ጋራጅ (መጋረጃ የሚጋርድ) ኾኖ ይኖራል። ሴት ብንወልድ፡ «ዕንጨት ሠብራ፥ ውኃ ቀድታ፡ ትርዳን!» አንልም፤ ለቤተ-እግዚአብሔር፡ መሶበ-ወርቅ ሰፍታ፣ መጋረጃ ፈትላ ትኑር!' ብለው፡ ብፅዓት ገቡ።

"ኢያቄምና ሓና፡ ከቀደሙት አያት ቅድመ-አያቶቻቸው ራእይ ይልቅ፡ የረቀቀ፡ ሌላ ራእይ፡ በየበኩላቸው ያያሉ፤ ይህም የኾነው፡ የሓምሌ አመ ሠላሳ ( የወሩ ማብቂያ) ዕለት ነበር።

"በዚች ዕለት ሌሊት፡ እርሷ፡ ለእርሱ፡ 'ፀምር (ከበግ ፀጉር የተሠራ፡ ማለፊያ ልብስ፣ ማለትም፡ በርኖስ) ሲያለብሱህ፣ መቋሚያህ አፍርታ፣ ፍጥረት ኹሉ ሲመገባት አየሁ!' ብላ፣

"እርሱ ደግሞ፡ ለእርሷ፡ 'ነጭ ርግብ፡ ሰባቱን ሰማያት ሠንጥቃ መጥታ፡ በራስሽ ላይ ስታርፍ፣ በቀኝ ጆሮሽ ገብታ፡ በማሕፀንሽ ስታድር አየሁ!' ብሎ፡ ኹለቱም፡ ያዩትን ራእይ ተጨዋውተዋል። ወደሕልም ፈቺም ኼደው፡ እንዲተረጉምላቸው ቢነግሩት፡ 'ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ!' ከማለት በቀር፡ አስተካክሎና አሟልቶ ሊፈታላቸው አልተቻለውም። እነርሱም፡ 'አንተስ አልፈታኸውም፤ ጊዜ ይፍታው!' ብለው፡ ወደቤታቸው ተመለሱ።

"እነርሱም፡ የራእያቸውን ፍጻሜ፡ በሃይማኖት ተስፋና በትዕግሥት ምግባር፡ እየተጠባበቁ ሳሉ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ሊቀ -መላእክት ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ፡ 'ደግ ልጅን ታገኛላችሁ! እርሷንም፡ በሊባኖስ ተራራ ትወልዳላችሁ!' ብሏቸው፤ ድንግል ማርያም፡ በፈቃደ አምላክ፣ በብሥራተ-መልአክ፡ ታኅሣሥ ፯ ቀን፡ የኢትዮጵያ መዲናና የታቦተ ጽዮን ማደሪያ በኾነችው፡ በአኵስም ተፀነሰች።

"ድንግል ማርያም በተፀነሰች ጊዜ፡ ብዙ ተአምራት ተደርጓል። ከእነዚህም መካከል፡ አንድ ኹለቱን፡ እዚህ ላይ እንጠቅሳቸዋለን፡-

"ለሐና፡ 'በርሴባ' የምትባል አክስት ነበረቻት፤ አንድ ዓይና ነች፤ 'ሐና! እግዚአብሔር፡ በረድኤት ጐበኘሽ መሰለኝ! ጡትሽ ጠቍሯል፤ ከንፈርሽም አርሯል፤' ብላ፡ ማሕፀኗን ዳስሳ፡ የጠፉ ዓይኗን ብታሸው፡ ስለበራላት፡ '**ብፅዓን ለኪ ሐና! እስመ እምፍጥረተ-ዓለም፡ አልቦ ዘከማኪ፡ ዘይፌውስ በከርሡ፡ አዕይንተ-ዕውራን።** ሐና ሆይ! የብፅዓን ክብር ይገባሻል፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ፡ እንደአንቺ፡ በማሕፀኗ፡ የዕውሮችን ዓይኖች ያዳነች ሴት የለችምና!' ብላ አሞገሰቻት።

"ይህን ድርጊት አብነት አድርገው፡ ሕሙማን ኹሉ፡ የሐናን ማሕፀን እየዳሰሱ፡ የሚፈወሱ ኾነዋል። ይልቁንም፡ 'ሳምንስ' የሚባል፡ ያጎቷ ልጅ ነበር፤ ሞተ። ሐና፡ በጣም ትወድደው ነበርና፡ ያልጋውን ሸንኮር ይዛ፡ እየዞረች ስታለቅስ፡ ጥላዋ፡ በአስከሬኑ ላይ ቢያርፍበት፡ ተነሥቶ፡ '**ሰላም ለኪ! ኦ እማ ለፀሐየ ጽድቅ! ዘትወልድ፡ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ!** የሰማይና የምድር ፈጣሪን የምትወልድ፡ የእውነት ፀሓይ እናት ሆይ! ሰላም፡ ለአንቺ ይኹን!' ብሎ፡ ከዚያ የሕልም ፈች የቀረውን ተርጉሞላታል።

# በአታ ለማርያም።

ሕፃን ማርያም፡ በጻድቃኑ ወላጆቿ ስእለት፡ እግዚአብሔር፟ን ልታገለግል የተሰጠች፡ የብፅዓት ልጅ ስለኾነች፡ እኒሁ ወላጆቿ፡ እንደሊቀ -መላእክቱ ቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ ከአኵስም ተነሥተው፡ ኢትዮጵያዊው የዘር ግንዳቸው መልከ- ጼዴቅ የቈረቈራት ኢየሩሳሌም ወደምትገኝባት፡ ወደምድረ-ከነዓን ተጉዘው፡ እንደኦሪቱ ሥርዓት፡ የእናቷን ማሕፀን፡ በብኵርናዋ በመክፈት፡ "**እምሊባኖስ ትወጽእ መርዓት! ሙሽሪት፡ ከሊባኖስ ትወጣለች!" የሚለው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፡ በዚያ፡ በሊባኖስ ተራራ በሚገኝ ዋሻ ውስጥ፡ **በመስከረም ፩ ቀን** ተወለደች።

**በተወለደች፡ በ፹ ቀኗ፡ በኅዳር ፳፩ ቀን፡** በወላጆቿ ዕቅፍ፡ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ፡ በቤተ-መቅደስ ከተገኘችበት ሥርዓት ቀጥሎ፡ አኹን ደግሞ፡ በሦስት ዓመቷ፡ ለኹለተኛ ጊዜ፡ እንደገና፡ ወደቤተ-መቅደስ ገብታ፡ በዚያ፡ የ፲፪ (ዐሥራ-ኹለት) ዓመታት ኑሮዋን የጀመረችበት ዕለት፡ ***ታኅሣሥ ፫ ቀን ኾኖ፡*** **«በአታ ለማርያም!»** ተብሎ የሚከበር ኾኗል።

በዚህ በዓል ዕለት፡ ሊታሰብና ሊነገር የሚገባው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የዜና መዋዕሏ የመጀመሪያ ክፍል፡ እንዲህ ነው፡-

"ከአኵስም የኼዱት፡ ኢያቄምና ሓና፡ ከጥንት ጀምሮ፥ በየጊዜያቱም፡ ከብሔረ ሙላዳቸው [ከትውልድ ምድራቸው]፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደኹለተኛዋ አገራቸው፡ ወደኢየሩሳሌም እየተጓዙ፡ በዚያች ምድር በሚኖሩ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘመዶቻቸው መካከል ተቀምጠው ሳሉ፡ ሕፃን ማርያም፡ በተወለደች በሦስት ዓመቷ፡ እናቷ ሓና፡ ባሏን ኢያቄምን፡ 'ይህች ብላቴና፡ ሆዷ፡ ዘመድ ሳይወድድ፤ አፏም፡ እህል ሳይለምድ፡ ለእግዚአብሔር በገባነው ቃል መሠረት፡ ወስደን፡ ለቤተ-መቅደስ አንሰጣትምን? «የሰጠ ቢነሣ! የለበት ወቀሳ!» እንዲሉ፡ አንዳች ነገር ብትኾንብን፡ ከልጃችንም፥ ከፈጣሪያችንም ሳንኾን እንዳንቀር!' አለችው።

"እርሱም፡ '«የእናትነት ፍቅርሽ፡ ይለቅልሽ!» ብዬ ነው እንጂ፡ እኔማ፡ ፈቃዴ አይደለምን?' አላት። ከፍቅሯ ጽናት የተነሣ፡ ሓና፡ ሕፃን ማርያምን፡ ከጭኗ አውርዳት አታውቅም ነበር፤ ምክንያቱም፡ አንድ ቀን፡ ብቻዋን፡ ከቤት ውስጥ ትታት፡ ከደጅ ወጥታ ስትመለስ፡ የእግዚአብሔር መልአክ ሠውሮባት፡ ጥራ፣ ግራ፡ አግኝታት ስለነበረ ነው፤ ከዚያ በኋላ፡ ያው እየመሰላት፡ ተለይታት አታውቅም።

"ወላጆቿ፡ ይህን ተነጋግረው እንዳበቁ፡ ሕፃን ልጃቸውን፡ ማርያምን ወስደው፡ ለቤተ-መቅደስ ሰጧት። በዚያን ጊዜ የነበረው ሊቀ -ካህናት፡ "ዘካርያስ" ይባላል፤ እርሱም፡ ስለምግቧ ነገር ሊያስወስን፡ መጥቅዕ (ደወል) አስደውሎና ሕዝቡን ሰብስቦ፡ በጉዳዩ ላይ እየተወያዩ ሣሉ፡ የእግዚአብሔር መልአክ ፡ ሊቀ - መላእክት ቅዱስ ሩፋኤል፡ የሰማይ ኅብስትና ጽዋ ይዞ፣ ከሰማይ ወርዶ፥ ረብቦ ታየ።

"በዚህ ጊዜ፡ ሊቀ -ካህናቱ ዘካርያስ፡ ለእርሱ የወረደለት ሀብት መስሎት፡ ሊቀበል ቢነሣ፡ ወደላይ ራቀበት፤ የሊቀ -ካህናቱ ተወራጅ፡ 'ስምዖን' ይባላል፣ እርሱም፡ ለመቀበል ቢነሣ፡ ወደላይ ራቀበት።

"ከዚህ በኋላ፡ 'ጥበበ-እግዚአብሔር፡ ምስጢሩ አይመረመርምና፡ ምናልባት፡ ለዚች ብላቴና የመጣ ሀብት እንደኾነ፡ ማን ያውቃል? እስኪ! እንየው!?' ብለው፡ ለብቻዋ አድርገዋት፡ ፈቀቅ ቢሉ፡ 'ድንኵል! ድንኵል!' እያለች፡ እናቷን ስትከተል፡ መልአኩ፡ ፈጥኖ ወርዶ፡ አንድ ክንፉን፡ አንጥፎ፣ አንድ ክንፉን ደግሞ፡ ጋርዶ፡ በሰው ቁመት ያህል፡ ከምድር አስለቅቆ፥ ከፍ አድርጓትና መግቧት ዐረገ።

"በዚህ ጊዜና ከዚህ የተነሣ፡ ካህናቱና ሕዝቡ፡ 'የምግቧ ነገር፡ እንዲህ ከተያዘልንማ፡ ከሰው ጋራ፡ ምን ያጋፋታል?' ብለው፡ ሕፃን ማርያምን፡ ከወላጆቿ ተቀብለው፡ ወደቤተ-መቅደስ አገቧት። በዚያም፡ ለዐሥራ-ኹለት ዓመታት ኖረች።" *[ከቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ፣ ከተገቢው አርትዖት ጋር።]*

## የታኅሣሥ ገብርኤል።

በዚሁ፡ በታኅሣሥ ወር፡ በ፲፱ኛው ቀን የሚውለው፡ የ"ታኅሣሥ ገብርኤል" በዓል፡ የሚከበርበት ምክንያት፡ እንዲህ ነው፡-

"እግዚአብሔር፡ ለኢትዮጵያዊነት ባበቃው፡ በሙሴ መሪነት፡ የእስራኤል ሕዝብ፡ በግብፅ አገር፡ ይማቅቁበት ከነበረው የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ አውጥቶ፡ ቤተ-መቅደሳቸውንና ከተማቸውን፡ ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፡ ቈርቍሮ በሠራት፡ በኢየሩሳሌም አድርገው፡ በምድረ-ከነዓን እንዲኖሩ አበቃቸው። እነርሱ ግን፡ በአካባቢያቸው ያሉትን አሕዛብ እየተከተሉ፡ አምልኮ ባዕድን በመፈጸም፡ አምላካቸውን እግዚአብሔርን አሳዘኑት። በነቢያቱ ቢመክራቸውና ቢገሥፃቸውም፡ በዚያ ኃጢአታቸው፡ እየጨመሩበት ከመኼድ በቀር፡ ከጥፋታቸው ተጸጽተው ሊመለሱ፡ ጨርሶ የማይቻል ኾነ።

"በዚህ መልክ፡ በፈጣሪያቸውና ከእርሱ ጋር በተጋቡት ቃል ኪዳናቸው ላይ፡ በሥውርና በገሃድ ያካኺዱት የነበረው ክህደት፥ ዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት፡ በመጨረሻ፡ ጽዋው ስለሞላ፡ እግዚአብሔር፡ ለዚህ ድርጊታቸው፡ ምስክር የኾነችውን፡ ታቦተ-ጽዮንን፡ ከእስራኤላዊው ንጉሥ፡ ከሰሎሞንና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት፡ ከማክዳ በተወለደው፡ በዳግማዊ ምኒልክ አማካይነት፡ በቅድሚያ፡ ወደኢትዮጵያ እንድትኼድ አደረገ።

"ከዚያ በኋላም፡ ያወረሳቸውን አገርና ከተማ ወርሮ ይበዘብዝ ዘንድ፡ አረማዊዉን ንጉሥ፡ ናቡከደነፆርን፡ ታላቅ የሠይፍ ኃይልን አስታጥቆ፡ ወደኢየሩሳሌም ላከ፤ ወራሪውም ንጉስ፡ ከነሠራዊቱ፡ በዚያ፡ የቅጣት ተልእኮውን እንዲፈጽም፣ ኃጢአተኛውንም የእስራኤል ትውልድ ፈጅቶ፡ የተረፉትን ደግሞ፡ በምርኮ፡ ወደምድሩ፡ ወደባቢሎን እንዲወስዳቸው፥ ለስደትም እንዲዳርጋቸው፡ አሠለጠነው።

"ለዚያ ስደት ከተዳረጉት አይሁድ መካከል፡ በሃይማኖታቸው የጸኑና በምግባራቸው የተጠናከሩ፥ አካኺዳቸው፡ ከነቢዩ ዳንኤል ጋር የኾነ፡ 'አናንያ፥ አዛርያና ሚሳኤል የተባሉ፡ መንፈሳውያን ወጣቶች ነበሩ። እነዚህ፡ 'ሠለስቱ ደቂቅ' የተባሉት፡ ሦስት ጐልማሶች፡ በዕውቀታቸውና በብልህነታቸው ተመርጠው፡ የንጉሡ ሹማምንት ኾነው ያገለግሉ ነበር።

"የኋላ ኋላ ግን፡ የሃይማኖትና የሥልጣን ወደረኞቻቸው፡ ባውጠነጠኑትና ለንጉሡ እስከደረሰው ሤራ፡ የአገሩን አማልክት እንዲያመልኩ፣ ንጉሡ ላቆመው ጣዖት እንዲሰግዱ፥ ያን ንጉሣዊ ትእዛዝ ተቀብለው ባያደርጉ፡ በዐዋጅና በአደባባይ እየነደደ ባለ፡ አስፈሪ የእሳት ነበልባል ውስጥ፡ የሚጣሉ መኾናቸውን የሚገልጽ፡ የፈተና ጥያቄ፡ ከንጉሡ ቀረበላቸው።

"እነርሱም፡ ለገንዘብና ለሹመት ጓጉተው፣ የንጉሡንም ቍጣ ፈርተው፡ አምላካቸውን የማይክዱ፣ ሃይማኖታቸውንም የማይለውጡ መኾናቸውን በመግለጽ፡ እንዲህ ሲሉ፡ በድፍረትና በቆራጥነት መለሱለት፡-

"'**ሀሎ አምላክነ ውስተ ሰማይ፣ ዘኪያሁ ናመልክ ንሕነ፤ ወይክል አድኅኖተነ እምእዴከ፣ ወእምእቶነ እሳት ዘይነድድ፤ ወያነግፈነ እምእዴከ፤ ንጉሥ! ከመ ታእምር፡ አ ንጉሥ! አምላክከሂ ኢና መልክ! ወለምስልሂ ዘወርቅ ዘአቀምከ፡ ኢንሰግድ!** ንጉሥ ሆይ! ቍርጡን እናሳውቅህ! ጣዖትህን አናመልክም። ላቆምኸውም የወርቅ ምስል አንሰግድም። እኛ፡ እርሱን የምናመልከው፥ የምንሰግድለት አምላክ፡ በሰማይ አለ። እርሱ፡ ከሚነድ እሳትና ከእጅህ፡ ሊያድነን ይቻለዋል፤ ንጉሥ! ከእጅህም ያስጥለናል።'

"በዚህ ጊዜ፡ የንጉሡ ቍጣ ስለነደደ፤ ፍርዱ እንዲፈጸምባቸው አዝዞ፡ ሦስቱም ገድለኞች፡ በሚነድደው እሳት ውስጥ ተጣሉ። ወደእሳቱ ሊጥሏቸው የወሰዱቸው ኃያላንም፡ በእሳቱ ነበልባል፡ ብርቱ ወላፈን እየተቃጠሉ ሞቱ።

"ወደእሳቱ ውስጥ፡ ታስረው የተጣሉት፡ እኒህ መንፈሳውያን አርበኞች ግን፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ እሳቱን አቀዝቅዞላቸው፡ በነበልባሉ መካከል፡ ወዲያ ወዲህ ሲመላለሱ ከመታየት በቀር፡ በአካላታቸው ቀርቶ፡ በየልብሳቸው ላይ እንኳ፡ አንዳችም ጉዳት ሳይደርስባቸው፡ ከተፈረደባቸው፡ የቃጠሎ ሞት ድነው፡ በደኅና ሊወጡ ችለዋል።

"ይህንም እውነታ፡ እንዲህ የሚለው፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ያረጋግጠዋል፡- '**ወአንከረ ናቡከደነፆር ንጉሥ፤ ወተንሥአ ፍጡነ፤ ወይቤሎሙ፡ ለመገብቱ፡- «አኮኑ ሠለስተ እደወ፡ ወደይነ ማእከለ እቶነ እሳት፡ እሱራኒሆሙ?»**

"'**ወይቤልዎ፡- «እወ! አ ንጉሥ!»** "

"'**ወይቤ ንጉሥ፡- «አንሰ እሬኢ ዝየ፡ አርባዕተ እደወ፡ ፍቱሓነ፤ ወያንሶሱዉ ማእከለ እቶነ እሳት፤ ወአልቦ ዘለከፎሙ። ወገጹ ለራብዓይ፡ ወልደ-እግዚአብሔር ይመስል።»**

"'**...ወሰገደ ንጉሥ ለእግዚአብሔር፡ በቅድሜሆሙ፤ ወአውሥአ ናቡከደነፆር፤ ወይቤ፡- «ይትባረክ እግዚአብሔር፡ አምላከ ሲድራቅ፣ ወሚሳቅ፣ ወአብደናጎ! ዘፈነወ መልአኮ! ወአድኃነ ነፍሳተ-አግብርቲሁ! እለ ተወከሉ ቦቱ! ወሜጡ ቃለ ንጉሥ! ወወሀቡ ነፍሳቲሆሙ፡ ከመ ኢያምልኩ፣ ወኢይስግዱ፡ ለካልእ አምላክ፡ ዘእንበለ ለእግዚአብሔር አምላኮሙ።**

"'**«ወአነሂ አዘዝኩ፡ ለኵሉ አሕዛብ፣ ወነገድ፣ ወበሓውርት፤ እመቦ ዘነበበ፥ ወጸረፈ፡ ላዕለ አምላከ ሲድራቅ፣ ወሚሳቅ፣ ወአብደናጎ፡ ትትኰነን ነፍሱ! ወይትበረበር ቤቱ! እስመ አልቦ አምላክ ካልእ፡ ዘያድኅን ከመዝ።»**

"'**ወሶቤሃ፡ ሤሞሙ፡ ንጉሥ፣ ለሲድራቅ፣ ወሚሳቅ፣ ወአብደናጎ፡ ላዕለ ግብረ በሓውርተ-ባቢሎን፤ ወአዕበዮሙ፣ወአኰነኖሙ፣ ለኵሉ አይሁድ፡ እለ ውስተ መንግሥቱ ሀለዉ።**

"'**ወይቤ፡ ናቡከደነፆር ንጉሥ፡ ለኵሉ አሕዛብ፣ ወነገድ፣ ወበሓውርት፣ ወለኵሉ ምድር፡- «ሰላም፣ ወዳኅና፡ ይብዛኅ ለክሙ! ተአምረ፥ ወመንክረ፡ ዘገብረ ሊተ፡ እግዚአብሔር ልዑል! አደመኒ በቅድሜየ፡ እንግርክሙ! እስመ ዓቢይ፥ ወጽኑዕ ውእቱ መንግሥቱ፣ መንግሥት ዘለዓለም። ወምኵናኑኒ፡ ለትውልደ-ትውልድ።»**

"'ንጉሡ ናቡከደነፆር፡ ይህን አደነቀ፤ ፈጥኖም ተነሣ፤ መኳንንቱንም፡- «ሦስት ሰዎችን አስረን፡ ወደእሳቱ ምድጃ መካከል፡ ጥለን አልነበረምን?» አላቸው።

"'እነርሱም፡- «ንጉሥ ሆይ! አዎን!» አሉት።

"'ንጉሡም፡- «እኔ፡ አራት ሰዎች፡ ተፈትተው፣ በእሳቱ መካከል ሲመላለሱ አያለሁ! እሳቱም፡ አልነካቸውም። የአራተኛው መልክ፡ የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል!» አለ።

"'...ንጉሡ ናቡከደነፆርም፡ በፊታቸው፡ ለእግዚአብሔር ሰገደ፤ እንዲህ እያለም፡ መለሰ፡- «ከፈጣሪያቸው፡ ከእግዚአብሔር በቀር፡ ‹ጣዖት አናመልክም! ለሌላ አምላክም አንሰግድም!› ብለው፡ ለንጉሡ፡ በድፍረት በመመለስ፡ ነፍሳቸውን ለእሳት አሳልፈው እስከመስጠት ወደቆረጡት፥ ወደታመኑበት አገልጋዮቹ፡ መልአኩን ሰድዶ፡ ሰውነታቸውን ያዳነ፡ የሲድራቅ፣ የሚሳቅና የአብደናጎ አምላክ፡ እግዚአብሔር፡ ይክበር! ይመስገን!

"'«እኔም፡ ‹እንዲህ፡ እንደእርሱ የሚያድን፡ ሌላ ፈጣሪ የሌለ መኾኑን ስላረጋገጥሁ፡ እንግዲህ፡ በሲድራቅ፣ በሚሳቅና በአብደናጎ አምላክ ላይ፡ አንዳች ክፉ ቃልን የተናገረ፥ የተሳደበም ሰው ቢገኝ፡ ሰውነቱ እንድትቀጣ፥ ቤት-ንብረቱም እንዲወረስ፡ በግዛቴ ለሚኖሩ ሕዝቦችና ነገዶች፥ አገሮችም ኹሉ፡ ይኸው ትእዛዜን አስተላልፌአለሁ።»

"'ንጉሡ፡ ይህን ዐውጆ፡ ወዲያው፡ ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና አብደናጎን፡ በባቢሎን አገሮች ሥራ ላይ ሾማቸው! በግዛቱ ውስጥ የሚኖሩትንም አይሁድ ኹሉ፡ ከፍ ከፍ አደረጋቸው፤ አሠለጠናቸውም።

"'ደግሞም፡ ንጉሡ ናቡከደነፆር፡ በግዛቱ ለሚኖሩ ሕዝቦችና ነገዶች፥ አገሮችና ለምድር ወገኖች ኹሉ፡ እንዲህ ሲል ዐወጀ፡- «ሕይወትና ሰላም ይብዛላችሁ! ገናና እግዚአብሔር፡ ያደረገልኝን ድንቅ ነገርና ተአምራት፡ እነግራችሁ ዘንድ፡ በፊቴ ደስ አሰኘኝ፤ እርሱ፡ ታላቅ፥ ጽኑም ነውና፤ መንግሥቱ፡ የዘለዓለም መንግሥት ናትና፤ የቸርነትና የፍትሕ አስተዳደሩም፡ ከትውልድ ወደትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የሚኖር ነው።»

"ንጉሡ፡ በእሳቱ ነበልባል ውስጥ ካያቸው ሰዎች መካከል፡ «**ወገጹ ለራብዓይ፡ ወልደ-እግዚአብሔር ይመስል።** የአራተኛው መልክ፡ የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል!» ያለው፡ ሊቀ-መላእክት ቅዱስ ገብርኤል መኾኑ፡ ከትውፊታችን ታውቋል። (ዳን. ፫፥ ፲፯-፲፰፤ ፺፩-፩፻።)

በሃይማኖት ሳይወላውሉ፡ በምግባር ተጠናክረው፡ እስከመጨረሻው፣ ይህም ማለት፡ የሞት ጽዋን ለመቀበል፡ ተዘጋጅቶና ቆርጦ እስከመቅረብ ድረስ፡ በጀመሩት ገድል፡ ጸንቶ መገኘት፡ የሚያስከትለው ውጤትና የሚያስገኘው ፍሬ፡ በነፍስና በመንፈስ ብቻ ሳይኾን፡ የሥጋ ሞትን ጭምር በማስቀረት፡ የምሕረት ሕይወትን፣ በክፉት ኃይላትም ላይ፡ ድልን የሚያቀዳጅ፡ የመላእክትን ተራዳኢነት የሚያተርፍ መኾኑን፡ በዚሁ፡ በታኅሣሥ ፲፱ ቀን የምናከብረው፡ "የታኅሣሥ ገብርኤል በዓል" ያስታውሰናል፤ ያስተምረናልም።

## ዘመነ ስብከት።

"ዘመነ-ስብከት"፡ በታኅሣሥ ፩ እና ፴ ቀኖች መካከል ባሉት፣ እያንዳንዳቸውም፡ በቅደም ተከተል፡ "**ስብከት**"፥ "**ብርሃን**"፥ "**ኖላዌ**" እና "**ጌና**" ተብለው በሚጠሩት፡ የእሑድ ሰንበታት የተጠቃለሉት፡ አራት ሳምንቶች ናቸው።

በእነዚህ ሰንበታትና ሳምንታት፡-

- የእግዚአብሔር፡ በሰውነት ወደዚህ ዓለም መጥቶ የመገለጡ፡ የምስጢረ-ሥጋዌው ነገር፣

- አመጣጡና መገለጡም፡ በቅድሚያ፡ እግዚአብሔር እም በተዋሓደቻት፡ በድንግል ማርያም፡ የፍቅር ምሥ ዋዐ-መድኃኒትነት፡ ያን፡ ራሱንና ፍጥረተ-ዓለሙን ያማሰነውን ሰውን፡ ለማዳንና በማዳን ስለመኾኑ፣

- ቀጥሎ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ እግዚአብሔር እም በተዋሓደቻት፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን፡ ከእግዚአብሔር አብ ተፀንሶ፡ በፍጹም ሰውነት፡ ከእርሷ በመወለድ፡ ለዝንተ-ዓለም፡ ሲዋጋው የኖረውን፡ የፀረ-እግዚአብሔሩን የዲያብሎስንና የሠራዊቱን፡ የክፋትና የሓሰት፥ የጥፋትና የሞት ጠንቆችና ጦርነቶች፡ በመለኮታዊዋ የእውነትና የፍቅር ሕማማተ-መስቀል፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፡ በድል አድራጊ ቤዛነት አስወግዶ፡ ዘለዓለማዊቷን የትንሣኤና የሰንበት ሰላምን መልሶ ለማጽናትና በማጽናት ስለመኾኑ፤

- በአጠቃላይ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ "**ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም!** ፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!" እያሉ፡ በምስጋና ጸሎታቸው የሚያሰሙት መዝሙራቸው፡ የዚህ እውነታ ማረጋገጫ ስለመኾኑ፣

- እግዚአብሔር ወልድ፡ "ኢየሱስ መሲሕ" በተባለበት ስሙም፡ በምድር ላይ እየተመላለሰ፡ ከክፉትና ከሓሰት በቀር፡ በሥጋም፣በነፍስም፥ በመንፈስም፡ እውነተኛውን ሰውኛ አኗኗር በመኖር፡ ለሰው ልጆች ኹሉ፡ ፍጹም አርአያና አብነት የኾነ ትምህርትን ስለማበርከቱ፣

- የኢየሱስ መሲሕ፡ ጥንተ ስቅለቱና የመስቀል ሞቱ ዕለት የኾነችው፡ የመጋቢት ፳፱ ቀኗ ዓርብ፥ የዘለዓለም ሰላምን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ አረጋግጦና አስተማምኖ ያጐናጸፈባት ስለኾነች፣ እንዲሁም፡ የመጋቢት ፴ ቀኗ ሰንበት፡ የመቃብር ዕረፍቱን፡ ያሳለፈባት ስለኾነች፣ ደግሞም፡ የሚያዝያ ፩ ቀኗ እሑድ፡ ይህችው፡ የጥንተ ኦኗ [የፀሓይዋ=የሰብአዊቷ] ሰንበት፡ በኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ፡ ወደቀደመው እግዚአብሔራዊና ጥንተ-ተፈጥሮአዊው ሰንበትነቷ ተመልሳ፡ ዘለዓለማዊ ህልውናዋን፡ እንዲህ የቀጠለች መኾኗን ያረጋገጠባት ስለኾነች፡ እነዚህን ሦስት ዕለታት፡ "**በዓለ ወልድ**" ብለን፡ በየሳምንቱ፥ በየወራቱና በየዓመቱ ልናዘክራቸው የሚገባን ስለመኾኑ፣

በነቢያት የተነገሩትን፡ የእግዚአብሔርን ትንቢታውያት ቃላት በመጥቀስ፡ ሰፊ ስብከትና ምዕዳን (ምክር) ይሰጥባቸዋል፤ የተስፋ ዝማሬ ይሰማባቸዋል፤ ስለሥጋዌ ምስጢርም፡ የቅኔያት ማዕበል ይወርድባቸዋል።

እነዚህን አርእስት በመከተል፡ በእነዚሁ ሳምንታት፡-

"**ፈኑ እዴከ፡ እምአርያም!** እጅህን፡ ከሰማይ ላክ!"

"**ፈኑ ብርሃነከ፥ ወጽድቀከ!** ብርሃንህንና እውነትህን ላክ!" እያሉ፡ የቀደሙት የእግዚአብሔር ሰዎች፡ ወደፈጣሪያቸው ያቀርቡት የነበረው፡ ያልተቋረጠ፡ የልመና ጸሎታቸው፡ ተሰምቶላቸው፡- "**አነ ውእቱ፡ ኖላዊ ኄር!** ቸር እረኛ፡ እኔ ነኝ!' የሚላቸውና "**የማነ እግዚአብሔር!** የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ!"፥ "**ብርሃን፡ ዘበአማን፡ ዘያበርህ፡ ለኵሉ ዓለም!** ለዓለሙ ኹሉ የሚያበራው፡ እውነተኛው ብርሃን!" የተባለው፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እነሆ፡ "**ሰው ኾኖ፡ በድንግል ማሕፀን ተፀነሰ! ተወለደ! እንደሰው፡ በምድር ላይ ተመላለሰ!**" በማለት፡ በመንፈስ፡ ወደኋላ ተመልሰን፡ የነቢያትን የተስፋ ጕዞ፡ በመንፈስ ጾምና ጸሎት፣ በዝማሬና በስባሔ እያካኼድን እንፈጽምባቸዋለን። (መዝ. ፻፵፫፥ ፯-፰፤ ፵፪፥ ፫፤ ፸፩፥ ፱-፲። ዮሐ. ፲፥ ፩-፲፬።)

\+ + +